የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፵፱
አዲስ አበባ ሰኔ ፰ ቀን ፲፱፻፺፮

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No. 49
ADDIS ABABA 15th June, 2004

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፬/፲፱፻፺፮ ዓ.ም

ከጀርመን ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ጋር ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና የሁለትዮሽ ጥበቃ ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ................ ገጽ ፪ሺ፮፻፶

## CONTENTS

Proclamation No. 404/2004

Investment Encouragement and Reciprocal Protection Treaty with the Federal Republic of Germany Ratification Proclamation ........... Page 2650

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፬/፲፱፻፺፮

## ከጀርመን ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ጋር ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና የሁለትዮሽ ጥበቃ ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አ ዋ ጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በጀርመን ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ መካከል ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና የሁለትዮሽ ጥበቃ ለመስጠት የሚያስችል ስምምነት ጥር ፲ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተፈረመ በመሆኑ፣

ስምምነቱ ሥራ ላይ የሚውለው በተዋዋይ ሀገሮች ሕጎች መሠረት ስምምነቱ መጽደቁን የሚያረጋግጡ ሰነዶች በዲፕሎማቲክ አካላት አማካኝነት ልውውጥ ከተደረገ በኋላ እንደሆነ በስምምነቱ በመገለፁ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት ከዚህ እንደሚከተለው ታውጇል::

## PROCLAMATION NO. 404/2004.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE TREATY SIGNED ON THE RECIPROCAL ENCOURAGEMENT AND PROTECTION OF INVESTMENTS WITH RTHE FEDERAL REPUBLIC OF GERMANY

**WHEREAS,** the Treaty on Encouragement and Reciprocal Protection of Investment between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Federal Republic of Germany is signed in Addis Ababa 19 January 2004;

**WHEREAS,** it is stipulated in the Treaty that it shall enter into force on the date of exchange of instruments of ratification through diplomatic channel;

**WHEREAS,** the House of the People's Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Treaty at its session held on 15th day of June, 2004

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ከጀርመን ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ ጋር ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና የሁለትዮሽ ጥበቃ ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፬፻፬/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ስምምነቱ ስለመጽደቁ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በጀርመን ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ መካከል ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና የሁለትዮሽ ጥበቃ ለመስጠት በአዲስ አበባ ከተማ ጥር ፲ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም የተፈረመው ስምምነት ፀድቋል፡፡

**፫. የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኃላፊነት**

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ስምምነቱን በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፰ ቀን ፲፱፻፺፮ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ፕሬዚዳንት**

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as "Investment Encouragement and Reciprocal Protection Treaty with The Federal Republic of Germany Ratification Proclamation No. 404/2004."

**2. Ratification of the Treaty**

The Treaty on the Encouragement and Reciprocal Protection of Investment signed in Addis Ababa on 19 January 2004 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Federal Republic of Germany is Ratified.

**3. Responsibility of the Ethiopian Investment Commission**

The Ethiopian Investment Commission is hereby empowered to implement this Treaty.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force as of 15th day of June, 2004

**Done at Addis Ababa, the 15th day of June, 2004**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት